# ወያኔ ኢህአዴግ ግንባር ቀደምና ሕዝባዊ አመራር እየሰጡ ባሉ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈፅመውን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት አጥብቀን እናወግዛለን፣

ወያኔ ኢሕአዴግ ባለፉት ሃያ ዓመታት ይህ ነው ተብሎ ለመግለጽ በሚያዳግት መልኩ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የተዋቀሩበትን የፖለቲካ፣ ያኮኖሚና የማህበራዊ ትሥሥር ምስጥ ይመስል እያነኮተ አገራችን ኢትዮጵያን ዛሬ ወደምትገኝበት አሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሷታል። የወያኔ የዘር ፖለቲካ አስተዳደር እንደ አፓርታይድ ሥርዓት በጫና የተጣለበት ሕዝብ ግን ከሥር ካስማ መሠረቱ፣ ከላይ ቁንጮ ጉልላቱ የሆነውን ኢትዮጵያዊነት አጥብቆ በመያዝ አንድነቷ ለማይናጋ ኢትዮጵያ፣ ለሠንደቅ አላማዋ፣ ለዘመናት ለቆየው አኩሪ ታሪኳና ላጠቃላኢ ህልውናዋ መከበር ከፍተኛ ተጋድሎና ትንንቅ እያደረገ ይገኛል።

በወያኔና በሕዝብ መካከል ያለው ግንኙነት ከዕለት ወደ ዕለት እየከረረ በመጣበትና በተለይም በሕዝብ ዘንድ እምቢኝ፣ አልገዛም፣ አሻፈረኝ የሚለው ተቃውሞ በዓይነትም ሆነ በመጠን እየጨመረ መምታት በወያኔ ካምፕ ውስጥ ክፉኛ መደናገጥና መርበትበትን ፈጥሯል። በተለይም በሰሜን አፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚታየው የሕዝባዊ ነውጽ ማዕበል ኢትዮጵያንም እያካለለ በመምጣቱ የተቁነጠነጠው የወያኔ አምባገነን ዘረኛ መንግሥት የፀረ ሽብርተኝነት ህግ በሚል ቀርጾ ባወጣው ፋሽስታዊ ሕግ አማካኝነት ያፈናና የእሥር ተግባሩን በተቃዋሚነት ጎራ በተሰለፉ ኢትዮጵያውያንና ሃሳባቸውን ያለፍርሃት በነፃነት በገለጹ የኪነት ባለሙያዎችና ታዋቂ ጋዜጠኞች ላይ እያስፋፋ መጥቷል።

ይህ ኢባስ ተብሎ የተፈራውን ሕዝባዊ አመጽ ከወዲሁ ለማጨናገፍ ሆን ተብሎ የሚፈፀም እኩይ ተግባር መሆኑን በመረዳት ባትዮጵያ ውስት ሆነ ካትዮጵያ ውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን በዕርዳ ተራዳ መንፈስ ድርጊቱን አትብቀን መቃወምና ለሰብዓዊ መብት መከበር፣ ለፍትህና ለነጻነት ለቆሙ መንግሥታት፣ ለሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ሁሉ በማሳወቅና እርዳታቸውን ማሰባሰብ እጅግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

እኛ ባኦታዋ-ካናዳ የምንኖርና የኢትዮ- ካናዳውያን ፎረም ለዲሞክራሲ በሚል መጠሪያ የተሰባሰብን ኢትዮጵያውያን፣

1ኛ. ሰሞኑን የሕዝብ ልጆች በሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ላኢ በወያኔ ኢህአዴግ የተወሰደውን ህገወጥ የእሥር፣ የአፈናና የ መቃ ተግባር አጥብቀን እናወግዛለን፣ ግላቦቹ ካላንዳች ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ ከእሥር እንዲፈቱም እንጠይቃለን።

2ኛ. በግለሰቦቹ መታሰር የተነሳ በቤተሰቦቻቸው ላኢ የደረሰውን የሃዘን ስሜትና የኑሮ ጫና በመረዳት አቅማችን በፈቀደው መጠን በሞራል፣ በገንዘብና በቁሳቁስ የሚያስፈልጋቸውን ለመርዳት ቃል እንገባለን።

3ኛ.የመድረክ ላንድነት አመራር አባላት ግንባራቸውን ሳያጥፉ እራሳቸውን ለትግሉ አሳልፈው በመስጠት በጀግንነትና በኩራት የተጋፈጡትን ዕውነታና የወሰዱትን አቋም እናደንቃለን፣ የሰጡትን ወቅታዊ ግምገማና በብሶት ምክናያት

የሚነሳን ሕዝባዊ አመፅ መቆጣጠር እንደማኢ.ቻል አስረግጠው ያስመሩበትን ግንዛቤ ትኩረት በመስጠት እራሳችንን ለሁኔታው ከወዲሁ ዝግጁ አድርገን በጀግንነት ለመቆም ተገቢውን ሁሉ እንደምናደርግ እናረጋግጥላቸዋለን።

4ኛ. የታሰሩት ኢትዮጵያውያን አላግባብና ሕገወጥ በሆነ መንገድ መሆኑን ለዓለም ዓቀፍ ህብረተሰብ፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ በፅሁፍ፣ በቃል፣ በሠላማዊ ሰልፍ፣ ተከታታይነት ያለው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ በማድረግና በየሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ገለጻ በማድረግ ድጋፍ በማሰባሰብ ከእስር እንዲፈቱ ካለማሳለስ እንተራለን።

5ኛ. ሕዝባዊ የተቃውሞ ድምፅን ለማፈንና ሽብርን በመንዛት የፖለቲካ ሥላታንን ለዘመናት እንደያዙ ለመቆየት በሕግ ሽፋን የለቀቀውንና ኢ-ዴሞክራሲያዊና ኢ-ሰብአዊ የሆነውን የፀረሽብርተኝነት እረቂቅ ሕግ እንዲሰረዝ አጥብቀን እንጤይቃለን።

6ኛ. ይህ ወቅታዊ ሁኔታው የወለደው ችግር የወያኔ አምባገነን ዘረኛ ሥርዐት እስካለ ድረስ ተባብሶ የሚቀጥል ስለሆነ ችግሩን ከሥር- መሠረቱ ለመፈንቀልና ለመጣል ይህን የወያኔ መንግሥት እስከ ግስንግሱ ማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑ ታምኖበት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅ ለእጅ በመያያዝ በጋራና በአንድነት መንፈስ የፀረ ወያኔን ዘመቻ ግፊታቸውን እንዲያጠናክሩ ይሪያችንን እናቀርባለን።

7ኛ. ባገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ የተለያዩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በመካከላቸው ያለውን አነስተኛ ልዩነት አቻችለው ወያኔና ፋሽስታዊ ሥርዓቱን ለማስወገድ፤ የግዛት አንድነቷ ተጠብቆ ሕዝቦች በነፃነትና በሕግ ፊት በዕኩልነት የሚኖሩባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በመስማማት የተናጠል እንቅስቃሴያቸውን አስተባብረው አገርና ወገንን በማስቀደም በሕብረት እንዲታገሉ ጥሪያችንን እንስተላልፋለን።

8ኛ. በተለያዩ ከክፍለ ዓለማት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን መሰል እርምጃዎችን በመውሰድ አገርና ሕዝብን ለማዳን በየክልላችን በተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ውስት በመግባት የዜግነት ግዴታችንን እንድንወጣ አትብቀን እንጠይቃለን።

ኢትዮጵያ በቆራት ልጆቿ ተጋድሎ ስርየትን ታገኛለች !

ኢትዮ- ካኔድያን ፎረም ለዲሞክራሲ ኦታዋ ካናዳ

October 7, 2011